# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ

## የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስተዳደር መመሪያ

ሰኔ 2014
አዲስ አበባ

# ይዘት

1 መግቢያ ..... 2
2 አጭር ርእስ ..... 2
3 የፓርቲው ራእይ፣ ተልእኮ እና ዓላማዎች እና የትግል ስልቶች ..... 2
4 የፓርቲው ሀገራዊ አደረጃጀት ..... 4
5 ጊዜያዊ አስተባባሪ ስለመመደብ ..... 4
6 ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስለመክፈት ..... 5
7 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠሪነት ..... 5
8 የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወጪ አሸፋፈን፤ ባንክ አካውንት ስለመክፈት እና የፋይናንስ አስተዳደር ..... 6
9 እቅድ እና ሪፖርት ዝግጅት ..... 7
10 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውድድር እና ሽልማት ..... 7
11 ብዝሀነትን ታሳቢ ያደረገ የጽ/ቤት አደረጃጀት ..... 8
12 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መደበኛ ስራዎች ..... 8
13 የፓርቲው የውጭ ሀገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ..... 10
14 ማህተም እና ደብዳቤ ልውውጥ ..... 10
15 የንብረት አያያዝ ..... 11
16 ባለድርሻ እና ተባባሪ አካላት ..... 12
17 የክልል/የዞን/የወረዳ/የከተማ አደረጃጀት ..... 12
18 መመሪያው የሚጸናበት ቀን ..... 13
አባሪዎች ..... 14
ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ..... 14
ማህተም ማስረከቢያ ቅጽ ..... 15

## 1 መግቢያ

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ)** እንደ አንድ ሀገር አቀፍ ፓርቲ በመላው ሀገሪቱ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የተሳካ ለማድረግ፣ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ዜጎች በቀላሉ የፓርቲው አባል የሚሆኑበትን መንገድ ለማመቻቸት በተለያዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና ከተሞች ጽ/ቤቶችን አደራጅቷል ወደፊትም በርካታ ጽ/ቤቶችን ያደራጃል፡፡

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ስራቸውን በተሳካ እና በተቀናጀ መንገድ ማካሄድ እንዲችሉ፣ የፓርቲውን አባላት፣ ደጋፊዎች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ከጽ/ቤቶቹ የሚጠብቁትን አገልግሎት በተቀላጠፈ መንገድ ማግኘት እንዲችሉ፣ ከዋና መስሪያ ቤት እና ከአቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር የሚኖራቸው የስራ ግንኙነት የተሳለጠ እንዲሆን ለማድረግ ግልጽ የአሰራር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2 አጭር ርእስ

**ይህ መመሪያ "የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር ስአኮ/02/001/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡**

## 3 የፓርቲው ራእይ፣ ተልእኮ እና ዓላማዎች እና የትግል ስልቶች

በየትኛውም ደረጃ ላይ የሚዋቀር የፓርቲው ቅርንጫፍ እንቅስቃሴ የፓርቲውን ራዕይ፣ ተልእኮ፣ ዓላማዎች እና የትግል ስልቶች ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት የፓርቲው ራዕይ፣ ተልእኮ፣ ዓላማዎች እና የትግል ስልቶች ቀጥሎ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 3.1 ራእይ እና ተልእኮ

የነእፓ ራእይ አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት የተረጋገጠባት፣ ዜጎች የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት ወዘተ ልዩነት ሳይደረግባቸው በብሄራዊ ጉዳዮች እኩል የሚሳተፉባትና ከልማቷ እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑባት የበለጸገችና ዲሞክራሲያዊት ሀገር እውን ሆና ማየት ሲሆን ድርጅታዊ ተልእኮው መልካም አስተዳደር እና የህግ የበላይነት የተረጋገጠባት፣ የፖለቲካ ስልጣን ከህዝብና ከህዝብ ብቻ የሚመነጭበት የፖለቲካ ባህል የዳበረባት፣ ዜጎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የሚጠቀሙባት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት ነው፡፡

### 3.2 ዓላማዎች

የፓርቲያችን ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

1. አካታች እና ዘላቂ ኢኮኖሚ በመገንባት ድህነትን መቀነስ ብሎም ማጥፋት፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትህን ማስፈን፣
2. በሀገሪቱ የመንግስት አስተዳደርና መዋቅሮች ውስጥ የመልካም አስተዳደር፣ የግልጸኝነትና ተጠያቂነት ስርአት እንዲጎለብት ማድረግ፣
3. የሰብዓዊና ዴሞክራሲዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ፣ የህግ የበላይነትን እውን ማድረግና ነጻ የፍትህ ስርዓት መገንባት፣
4. የብሄሮችና ብሄረሰቦችን ቋንቋና ባህል በእኩልነት ለማበልጸግ፣ ሁሉንም የሀገራችንን ክልሎች ልማት ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ የሚያስችል እውነተኛ የፌደራል ስርአት መገንባት፣

5. አካባቢ መጠበቅ፣ መንከባከብና ማበልጸግ፣ ምቹ የስራ እና የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር፣
6. ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማስፋፋት፣ በተፈጥሮና ማህበረሰብ ሳይንስ መስኮች ጥናትና ምርምርን መደገፍ፣
7. የገጠር ኢንዱስትሪን ማበረታታትና ማስፋፋት፣ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚውን ማዘመን፣
8. ዜጎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን በጥራት፣ በስፋትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ፣
9. ሴቶችና ወጣቶች በሀገር ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ እምቅ ኃይላቸውን መጠቀም፣
10. ህጻናት፣ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን መብቶችና ጥቅሞች ማስከበር፣
11. በአፍሪካ ቀንድ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ትስስርን ማበረታታትና መደገፍ፣ በክልሉ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን አስተዋፅዖ ማድረግ፣
12. ኢትዮጵያ በአፍሪካና በዓለም ዓቀፍ መድረኮች ተሰሚነትና የማይተካ ሚና እንዲኖራት ማስቻል፣ የኢትዮጵያን የውጭ ገጽታ ማሻሻል፡፡

### 3.3 የትግል ስልቶች

**ሚዛናዊነት እና ምክንያታዊነት፡** የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ መሰረታዊ መገለጫ ሚዛናዊነት እና ምክንያታዊነት ነው፡፡ የነእፓ የፖለቲካ ርእዮተ ዓለም፣ ፖሊሲ እና ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም በየጊዜው የሚወስዳቸው አቋሞች ሚዛናዊነትን እና ምክንያታዊነትን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ነእፓ ዋልታ ረገጥነት፣ የፖለቲካ ጽንፈኝነት፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ወገንተኝነት ሀገራችን ዛሬ ላይ ለደረሰችበት ፖለቲካዊ እና ማህበረ-ኢኮኖሚ ምስቅልቅል ዋነኛው ምክንያት ነው ብሎ ያምናል፡፡ ነእፓ ከዚህ አይነት የተዛባ የፖለቲካ አቋም በራቀ መልኩ በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር "ወርቃማውን አማካይ/Golden mean" ይከተላል፡፡ ነእፓ በየትኛውም የፓርቲ መወቅር/አደረጃጀት፣ በማንኛውም ጊዜ እና ወቅት የሚከተለው አቅጣጫ፣ የሚወስደው አቋም፣ የሚሰራቸው ስራዎች፣ የሚያስተላልፋቸው መልእክቶች ሚዛናዊ እና ምክንያታዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡

**በመግባባት ላይ የተመሰረተ ከፍጥጫ፣ ከሴራና መጠላለፍ የራቀ የፖለቲካ ትግል፡** ፓርቲያችን ከማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ወይም ድርጅት ጋር በኃላፊነትና በሀገር ፍቅር ስሜት ይሰራል፡፡ ሀገራችንን እና ህዝባችንን በሚጠቅሙ ጉዳዮች ዙሪያ ማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ወይም ፕሮግራም ካለው የፖለቲካ ድርጅት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

**አካታችነት**፡ የህዝባችንን የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የባህል ብዝሃነት ከግምት ውስጥ በማስገባት አካታችነት የነእፓ አንዱ እና ዋነኛ ምርህ ነው፡፡ በመሆኑ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በደረጃጀት፣ በአባልነት እና በአመራር ስብጥር ወዘተ አካታች አሰራርን የሚከተል ሲሆን በዜጎች መካከል የብሄር፣ የሀይማኖት፣ የባህል፣ የጾታ ወዘተ ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም የሀገራችንን ህዝቦች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማገልገል ይሰራል፡፡

**ተፈጥሯዊ ለውጥ፡** በሀገራችን ያለው የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ቢያንስ ላለፉት በርካታ አስርተ-ዓመታት ሲጠራቀሙና ሲደራረቡ የቆዩ በመሆናቸው በአንድ ጀንበር እንደማይቀረፉ ፓርቲያችን ይገነዘባል። በመሆኑም ነእፓ በሀገር ደረጃ እንዲመጡ የሚፈለጉ ለውጦች የማህበረሰቡን የእድገት ደረጃ በጠበቀ መልኩ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ለመቀየር ይሰራል፡፡

**አብሮ ማሸነፍ፡** እውነተኛ ማሸነፍ የሀገር እና የህዝብ ማሸነፍ መሆኑን **ነእፓ** ይረዳል፡፡ በመሆኑም በፖለቲካ እንቅስቃሴአችን ከድርጅታዊ ድል እና ስኬት ይልቅ የሀገርንና የህዝባችንን ድልና ስኬት እናስቀድማለን፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የፓርቲያችን

ውጤታማነትና ስኬት በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ውድቀት ላይ ሳይሆን አብሮ በማደግ እውነተኛ የአጋርነት ስሜት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

**ህዝብን ማገልገል፡** የአንድ የፖለቲካ እንቅስቃሴና የፖለቲካ ስልጣን ትልቁና የመጨረሻ ግብ ሀገርንና ህዝብን ማገልገል ነው፡፡ ህዝብን እንዲያስተዳድሩ የሚወከሉ የፓርቲና የመንግስት ኃላፊዎች፣ አስተዳዳሪዎችና ቢሮክራቶች ከድሀው ህዝብ "ከእጅ ወደ አፍ" ገቢ ከሚሰበሰብ ግብር የሚከፈላቸው ናቸው፡፡በመሆኑም በየትኛውም የኃላፊነት ደረጃ የሚገኙ የፓርቲያችን አባላት የህዝብ አገልጋይ ሆነው የመስራት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

**እውነተኛነት እና ታማኝነት፡** ኢትዮጵያውያን ለመልካም ስነ-ምግባር እና ግብረገብነት ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን፡፡ ህዝባችን በማህበራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለእውነተኛነት፣ ቅንነት እና ታማኝነት ላቅ ያለ ክብር ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የፓርቲያችን ተርታው አባልም ሆኑ አመራሮች ሀገራችንና ህዝባችንን በእውነተኛነት፣ በታማኝነት እና በፍቅር ያገለግላሉ፡፡

**በትብብር መስራት፡ ነእፓ** የዴሞክራሲ ስርዓትን ለመገንባት፣ ሀገራዊ መግባባትን ለማጠናከር፣ ጤናማ የፖለቲካ ውድድርን እውን ለማድረግ፣ የሀገራችንን የፖለቲካ ፓርቲዎች አቅም ለመገንባት ብሎም የፓርቲያችንን ራእይና ዓላማዎች በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት የሚያግዝ ሆኖ ሲገኝ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

## 4 የፓርቲው ሀገራዊ አደረጃጀት

**የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** አደረጃጀት በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን ወይም ክፍለ-ከተማ፣ በወረዳ ወይም ከተማ፣ ቀበሌ፣ ንኡስ ቀበሌ እና ተቋማት ላይ የሚዘረጋ ሲሆን የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡፡

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. ብሄራዊ ምክር ቤት
3. ብሄራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
4. የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን
5. ሊቀመንበር
6. ምክትል ሊቀመንበር
7. ዋና መስሪያ ቤት
8. የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች
9. የዞን ወይም ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች
10. የወረዳ ወይም ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች
11. የቀበሌ እና ንኡስ ቀበሌ አደረጃጀት
12. የተቋማት አደረጃጀት

በዚህ መሰረት ከማዕከል እስከ ንኡስ ቀበሌ እንዲሁም በተቋማት ደረጃ የሚዋቀረው የፓርቲው አደረጃጀት ከላይ የተመለከተውን የፓርቲው ጠቅላላ አደረጃጀት የተከተለ ይሆናል፡፡

## 5 ጊዜያዊ አስተባባሪ ስለመመደብ

በአንድ አካባቢ የፓርቲውን አደረጃጀት ለመፍጠር እንደየ ደረጃው ከፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ወይም ከነእፓ የክልል ስራ አስፈጻሚ ጊዜያዊ አስተባባሪ ይሰየማል፡፡ የክልል ጊዜያዊ አስተባባሪዎች ከፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት የሚመደብ ሲሆን

የዞን፣ የወረዳ እና የከተማ ጊዜያዊ አስተባባሪዎች በክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመደባሉ፡፡ የፓርቲው የክልል አደረጃጀት ባልተፈጠረባቸው ክልሎች የፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ከክልል በታች ያሉ አደረጃጀሮችን ለመፍጠር ጊዜያዊ አስተባባሪ ሊመድብ ይችላል፡፡ የጊዜያዊ አስተባባሪዎች ቁጥር እንደየ አካባቢው ሊለያይ ይችላል፡፡

በየደረጃው የሚሰየሙ ጊዜያዊ አስተባባሪዎች እጅግ ቢዘገይ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ አባላትን በማፍራት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረ ቋሚ አደረጃጀት ይፈጥራል፡፡ ቋሚ አደረጃጀቶች በአባላት የሚመረጡ አመራሮች ይኖሩታል፡፡ ቋሚ አደረጃጀት ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ የጊዜያዊ አስተባባሪዎች ኃላፊነት ያበቃል፡፡

## 6 ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስለመክፈት

በአንድ ከተማ ወይም ወረዳ የፓርቲውን ቅርንጫፍ ለመፍጠር የአባላት ብዛት ቢያንስ 20 (ሀያ) ሊሆን ይገባል፡፡ በአካባቢው የሚገኙ አባላት በመሰብሰብ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የማእከላዊ ኮሚቴ እና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣሉ፡፡ የማዕከላዊ ኮሚቴ እና ስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት ብዛት እንደ ሁኔታው ከፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ወይም ከፓርቲው የክልሉ ቅርንጫፈ ጋር በመነጋገር መወሰን ይቻላል፡፡

ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሲቋቋም የፓርቲው ዋና መ/ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፍ መ/ቤት ለዞን ወይ ለወረዳው ወይም ለከተማው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አስፈላጊ የፓርቲውን ሰንዶች ቅጂ (የፓርቲው የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንድ፣ ማኒፌስቶ ወዘተ ) እንዲሁም የአባልነት መታወቂያ፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስም የተዘጋጀ ማህተም፣ የባንክ አካውንት መክፈቻ ደብዳቤ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ያቀርባል፡፡

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይህንን መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የፓርቲውን ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ ስራቸውን ያካሂዳሉ፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚከፈት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሙሉ አድራሻ በነኢፓ የክልል ቅርንጫፎች በኩል ለፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኝ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማሳወቅ ይገባል፡፡

## 7 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠሪነት

በፓርቲው መረዳደሪያ ደንብ መሰረት የፓርቲው ቅርንጫፎች ተጠሪነት እንደሚከተለው ይሆናል፡

- የቀበሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- የወረዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለዞን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- የዞን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ይሆናል

ከላይ በተመለከተው ቅደም ተከተል በሁሉም ደረጃ የፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ባልተሟሉበት አካባቢ፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠሪነት በቅርብ ለሚገኘው የበላይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## 8 የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወጪ አሸፋፈን፤ ባንክ አካውንት ስለመክፈት እና የፋይናንስ አስተዳደር

### 8.1 የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወጪ አሸፋፈን

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** እስከ አሁን ያደራጃቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እውን የሆኑት በየአካባቢው በሚገኙ የፓርቲው አባላት እና ደጋፊዎች የፋይናንስ እና የማቴሪይል ድጋፍ ሲሆን በቀጣይ የሚከፈቱ ጽ/ቤቶችን በዚሁ አሰራር የሚደራጁ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር በተለያዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና ከተሞች የፓርቲውን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለመክፈት በየአካባቢው የሚገኙ አደራጆች ለጽ/ቤት ማቋቋሚያ የሚሆን ገንዘብ እና መሰረታዊ የጽ/ቤት ቁሳቁሶችን ከአባላት እና ደጋፊዎች ማሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በራስ ኃይል መክፈት እና ማደራጀት ፓርቲው በአጭር ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለማደራጀት የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለማደራጀት በፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፎች ላይ የሚፈጠረውን የፋይናንስ ጫና በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ እና ቀበሌ ነዋሪዎች በየአካባቢያቸው ለሚያደርጉት ድርጅታዊ እንቅስቃሴ በፋይናንስ ራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱ፣ የፓርቲው አደረጃጀት ዘላቂ እንዲሆን እና አባላት የፓርቲው ባለቤት መሆናቸውን በተግባር የሚያረጋግጡበትን እድል ይፈጥራል፡፡

ሀገርን እና ህዝብን ለማገልገል የሚደረግ የፖለቲካ ትግል እና የሚከፈል ዋጋ የአባላትን ጊዜ፣ ጉልበት፣ እውቀት እና ገንዘብ ይሻል፡፡ በመሆኑም ነእፓ በመላው የሀገሪቱ ክፍል አደረጃጀቱን እንዲዘረጋ እና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ሁሉም የፓርቲው አባላት በአካባቢያቸው የሚካሄደውን እንቅስቃሴ በገንዘብ የማገዝ ድርጅታዊ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### 8.2 የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባንክ አካውንት ስለመክፈት

የክልል፣ የዞን፣ የከተማ/ወረዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከተቋቋሙ በኃላ ከፓርቲው ዋና መ/ቤት በሚጻፍ ደብዳቤ በሁለት ፈራሚዎች ጣምራ ፊርማ የሚንቀሳቀስ የባንክ አካውንት ይከፈታል፡፡ የቅርንጫፉ ባንክ አካውንት ሊቀመንበሩ እንደ አመቺነቱ ከምክትል ሊቀመንበሩ ወይም ከፋይናንስ እና አስተዳደር ኃላፊው ጋር በጣምራ ፊርማ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

### 8.3 ፋይናንስ አስተዳደር

የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ማንኛውም ዓይነት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የፓርቲውን የፋይናንስ ደንብ እና አጠቃላይ የሀገሪቱን የፋይናንስ ህጎች የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡ ከፓርቲው የፋይናንስ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ነጥቦች ልዩ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ማናቸውም ዓይነት ገንዘብ የፓርቲውን የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥ መሰብሰብ አይቻልም፣
- ማንኛውም የፓርቲው ገቢ፣ የአባላት መዋጮ ወይም ድጋፍ በህጋዊ ደረሰኝ ከተሰበሰበ በኃላ በፓርቲው የባንክ አካውንት ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

- ማናቸውም የፓርቲው ህጋዊ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች በፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት በኩል ታትመው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይሰራጫሉ፡፡ ማንኛውንም አይነት ደረሰኝ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማሳተም ህገወጥ ሲሆን በህግ ያስጠይቃል፡፡
- የአባላት መዋጮን  ለመከታተል በፓርቲው የተዘጋጀውን የኤክሴል ፕሮግራም በመጠቀም ቢያንስ በየሩብ አመቱ በፓርቲው የክልል ቅርንጫፍ በኩል ለፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ይላካል፡፡
- ቅርንጫፎች ጽ/ቤቶች ለጥቃቅን ወጪዎች (Pitty cash) አገልግሎት በጣም አነስተኛ ገንዘብ በቅርንጫፉ ካዝና ሊቀመጥ ይቻላል፡፡ የገንዘቡ መጠን በቅርንጫፉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይወሰናል፡፡

# 9 እቅድ እና ሪፖርት ዝግጅት

## 9.1 እቅድ ዝግጅት

እያንዳንዱ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ ወይማ የቀበሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመታዊ እቅዱን አዘጋጅቶች በቅርብ ለሚገኘው የፓርቲው የበላይ አካል ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በየደረጃው የሚዘጋጁ የፓርቲው ዓመታዊ፣ የግማሽ ዓመት ወይም የሩብ አመት እቅዶች ወጥነት ይኖራቸው ዘንድ የፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የእቅድ ማዘጋጃ ቅጽ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ የቅርንጫፉ አመታዊ እቅድ የበጀት አመቱ ከመጀመሩ (ሀምሌ 1) በፊት ቀድሞ ለክልል ወይም ለፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ሊቀርብ ይገባል፡፡

## 9.2 ሪፖርት

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መደበኛ ሪፖርቶችን ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሪፖርቶቹ የሰራ እና የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን የሚያጠቃልሉ ሲሆን የሚከተሉትን ነጥቦች ማካተት ይኖርበታል፡

- አዲስ አባላት ዝርዝር
- የፋይናንስ እንቅስቃሴ (ገቢ እና ወጪ)
- ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች፡፡

በሁሉም ደረጃ ላይ የሚገኝ የነእፓ ቅርንጫፍ የሩብ ዓመት ሪፖርት፣ ሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ እጅግ ቢዘገይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ ይኖርበታል፡፡ የነእፓ የበጀት ዓመት ከሀምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ሲሆን የሩብ ዓመት ሪፖርቶችም ይህንኑ ታሳቢ ያደረጉ ይሆናል፡፡

**ማስታወሻ፡** ከዚህ መመሪያ መጨረሻ ገጽ ላይ የሪፖርተ ማቅረቢያ ናሙማ ቅጽ የተያይዘ ሲሆን፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማራጭ የሪፖርት ቅጽ መጠቀም ይቻላል፡፡

# 10 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውድድር እና ሽልማት

የፓርቲውን የክልል ቅርንጫፎች ለማበረታታት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል ጤናማ ውድድር ለመፍጠር የነእፓ ዋና መስሪያ ቤት የክልል ቅርንጫፎችን የስራ አፈጻጸም ያወዳድራል የተሻለ የስራ አፈጻጸም ላላቸው ቅርንጫፎች ሽልማት ይሰጣል፡፡ የማወዳደሪያ ነጥቦቹ በአመት የተመዘገቡ አዲስ አባላት ብዛት እና ቅርንጫፉ ያሰበሰበው ገንዘብን ጨምሮ በፓርቲው ስራ አስፈጻሚ ይዘጋጃል፡፡

## 11 ብዝሀነትን ታሳቢ ያደረገ የጽ/ቤት አደረጃጀት

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ዜጎች ብሄርን፣ ቋንቋን፣ እምነትን ወዘተ መሰረት ያደረገ ልዩነት ሳይደረግባቸው በብሄራዊ ጉዳይ እኩል ተሳታፊ እና ከሀገር ልማት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚታገል ፓርቲ ነው፡፡ ይህን ድርጅታዊ ራእይ እውን ለማድረግ ቅድሚያ በድርጅቱ ውስጥ ብዝሀንትን መቀበል እና መተግበር፣ ከብዝሀንት ጋር የሚቃረኑ አሰራሮች እንዳኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት በየደረጃው የሚቋቋሙ የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ጽ/ቤቶች አደረጃጀት የብሄር፣ የእምነት የጾታ ወዘተ ብዝሀነትን ታሳቢ ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በየደረጃው የሚቋቋሙ የፓርቲው ጽ/ቤቶች ሁሉም የፓርቲው አባላት ማህበራዊ እሴቶች በእኩልነት የሚታዩበት አደረጃጀት እና ውቅር ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 12 የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መደበኛ ስራዎች

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚከተሉት መደበኛ ክንውኖች እንዲኖራቸው ይጠበቃል፤ ወርሀዊ የአባላት ስብሰባ፣ የአዲስ አባላት ምዝገባ ቀን፣ የወጣቶች የስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ ማህበራዊ ኃላፊነት፡፡ እያንዳንዱን ክንወን አስመልክቶ አጭር መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፣

1) ***የውይይት መድረኮች፡*** ሁሉም የነእፓ ቅርንጫፎች አካባቢያዊ፣ ክልላዊ ወይም ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት፣ ምክክር የሚካሄድበት መድረክ በመደበኛነት ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡ በውይይቱ ላይ የፓርቲው አመራሮች፣ አባላት፣ ደጋፊዎች፣ እንዲሁም በውይይቱ ላይ መሳተፍ ሀሳብ መስጠት እና መማር ፍላጎት ያላው/ያላት ማንኛውም ነዋሪ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ለውይይቱ እሴት ይጨምራሉ ብሎ የቅርንጫፉ አመራርር ካመነ፣ የሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲ አባላትን ሊጋበዙ ይችላሉ፡፡ የውይይት መድረኮቹ ዓላማ፣

   - በፓርቲው ፕሮግራም፣ ፖሊሲ እና ፕሮግራሞች ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ማስቻል፣
   - አባላት በሚገኙበት አካባቢዎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የሰላም እና ጸጥታ፣ የልማት ወዘተ ጉዳዮች ዙሪያ መወያየት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አቋም ለመያዝ፣
   - ፓርቲው በተለያዩ ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በሚይዛቸው አቋሞች ዙሪያ ለመወያየት፣

2) ***ስልጠና፡*** እያንዳንዱ ቅርንጫፍ አባላት እና አመራሮች በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ ስልጠና ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ የሚዘጋጁት ስልጠናዎች ሁለት አይነት ይዘት ያላቸው ሲሆን፣ የመጀመሪያው በፓርቲው ርእዮተ ዓለም፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ማኒፌስቶች፣ የፓርቲ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ አደረጃጀት ወዘተን ይመለከታል፡፡ በፓርቲ ሰነዶች ዙሪያ በቂ ስልተና የወሰዱ አባላት እና አመራሮች በፓርቲው የስልጠና መርሀ ግብር መሰረት በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠናዎችን ሊወስዱ ይገባል፡፡ ድርጅታዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰጡ ስልጠናዎች በፓርቲው የዞን፣ የክልል ወይም የማእከል አመራሮች የሚሰጥ ሲሆን፣ በተጨማሪ ርእሶች ዙሪያ የሚሰጡ ስልጠናዎች በአካባቢው ከሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት/ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ሊሰጥ ይችላል፡፡ የፓርቲውን የምሁራን/ዩኒቨርስቲ አደረጃጀት በመጠቀም ፍቃደኛ ምሁራንን ማግኘት ይቻላል፡፡ ስልጠና የሚሰጡ ምሁራንን በማፈላለግ የፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ድጋፍ ሊያደርግ ይቻላል፡፡

3) ***የአዲስ አባላት ምዝገባ ቀን፡*** እያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አባላትን በስፋት እና በብዛት የሚመዘግቡበት በወር አንድ ቀን ይመድባሉ፡፡ ይህ ቀን የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ለአብዛኛው ነዋሪ ምቹ ሊሆን ይገባል፡፡

4) ***የወጣቶች የስፖርታዊ እንቅስቃሴ፡*** የነእፓ ቅርንጫፎች እንደ አመችነቱ በወር ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ አባላት፣ ደጋፊዎች እና በአጠቃላይ የአካባቢው ማህበረሰብ የሚሳተፍበት ስፖርታዊ ፕሮግራም ያዘጋጃሉ፡፡ የሚዘጋጀው ስፖርታዊ ፕሮግራም አይነት፣ የሚዘጋጅበት ቀን እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የአካባቢውን፣ የአየር ጸባይ፣ ባህል፣ የከተማውን እድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፣

5) ***ማህበራዊ ኃላፊነት፡*** የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከዋናው የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ጎን ለጎን ማህበረሰብን የማገልገል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት እያንዳንዱ የነእፓ ቅርንጫፍ አባላቱን፣ ደጋፊዎችን እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበር የአካባቢውን ተጨባጭ መሰረት ባደረገ ሁኔታ የህብረተሰቡን መሰረታው ችግሮች ለመቅረፍ በሚደረግ እንቅስቃሴ ጉልህ ተሳትፎ እና አስተዋጾ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ፓርቲው የሚሳተፍባቸው ማህበራዊ ኃላፊነቶች ከአካባቢ አካባቢ ሊለያዩ ቢችልም የሚከተሉትን እንቅስቃሴዎች እንደ መነሻ መውሰድ ይቻላል፤ አካባቢ ጥበቃ፣ ደም ልገሳ፣ የአካባቢ ጽዳት፣ አቅመ ደካሞችን መንከባከብ፣ የገበሬ ሰብል መሰብሰብ፣ ወዘተ።

6) ***ሻይ ቡና ፕሮግራም፡*** የነእፓ የሻይ ቡና ፕሮግራም በፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመደበኛነት የሚካሄድ ፕሮግራም ነው፡፡ በሻይ ቡና ዝግጅት ላይ ላይ የነእፓ የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ማኒፌስቶች፣ ወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የፓርቲው እይታ፣ የፓርቲ ቀጣይ እቅዶች ወዘተ ይቀርባሉ፡፡ የፕሮግራሙ ዓላማ የከተማው ነዋሪዎች ነእፓን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስቻል፣ የፓርቲው አባል እንዲሆኑ ማሳመን፣ አባል መሆን ካልቻሉ ደጋፊ እንዲሆኑ ማስቻል ናቸው፡፡ የሻይ ቡና ፕሮግራም ከፓርቲው ጽ/ቤት ውጪ በመሰብሰቢያ አዳራሾች ወይም በአባላት መኖሪያ አካባቢ ሊካሄድ ይችላል፡፡

7) ***የሩብ አመት፣ እና የግማሽ አመት ስብሰባ፡*** በፓርቲው አሰራር፣ አደረጃጀት፣ ስኬቶች እና ተግዳሮቶች ወዘተ ዙሪያ ምክክር የሚደረግበት ስብሰባ በየሶስት ወሩ ሊካሄደ ይገባል፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ የሚሳተፉት የፓርቲው ዓባላት ብቻ ናቸው፡፡ በእንዚህ ስብሰባዎች ላይ የቅርንጫፉ የእቅድ ክንውን እንዲሁም የፓርቲው የስራ ኃላፊዎች የስራ ክንውን ግምገማ በማካሄደ ድክመቶች እንዲታረሙ ይደረጋል፡፡

8) ***ዓመታዊ መደበኛ ጉባኤ፡*** እያንዳንዱ ቀበሌ፣ ከተማ፣ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል፣ በስሩ የሚገኙ አባላት የሚሳተፉበት ዓመታዊ ጉባኤ ሊያካሂድ ይገባል፡፡ የቅርንጫፉ መደበኛ ዓመታዊ ጉባኤ ወቅቱን ጠብቆ ሊካሄድ ይገባል፡፡በአመታዊ ጉባኤዎች ላይ የቅርንጫፍ አመታዊ የስራ እንቅስቃሴ በጥልቀት ይገመገማል፣ የስራ ዘመናቸውን ባጠናቀቁ አመራሮች ምትክ አዳዲስ አመራሮች ምርጫ ይካሂዳል፡፡ በከተማው/በወረዳው ዓመታዊ ጉባኤ ላይ በአካባቢው ያሉ የፓርቲውን አባላት ብዛት ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ ከቀበሌዎች የሚወከሉ አባላት ይሳተፋሉ፡፡ በየደረጃው በሚካሄዱ ዓማታዊ ጉባኤዎች ላይ በቅርብ የሚገኘው የፓርቲው የበለይ አደረጃጀት በመገኘት የጉባኤውን ሂደት ሊታዘብ ይገባል፡፡ በጉባኤው ላይ የሚገኘው የበላይ አካል ታዛቢ የቅርንጫፉ ጉባኤ በፓርቲው ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት መካሄዱን፣ የአመራሮች ምርጫ ነጻ እና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መካሄዱን ይታዘባል፡፡ በአመታዊ ጉባኤዎች አስተዳደራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት በማድረግ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

9) ***የአካባቢ ጉዳዮችን በቅርበት መከታተል፣ አስፈላጊ ሲሆን ለፓርቲው የበላይ አካል ማሳወቅ፡*** የነእፓ የክልል ቅርንጫፎች በየአካባቢያቸው የሚካሄዱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ፣ የመልካም አስተዳደር እና የጸጥታ ጉዳዮች በንቃት እና በጥልቀት ሊከታተሉ እና ሊተነትኑ ይገባል፡፡ የክልል ቅርንጫፎች ክልላዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከፓርቲው ዋና መ/ቤት ጋር በመነጋገር የአቋም መግለጫ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የአቋም መግለጫ ከማውጣታቸው በፊት የሚወስዱት አቋም ከፓርቲው ፖሊሲዎች እና ፕሮጋራሞች እንዲሁም አጠቃላይ እሳቢዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ረቂቅ መግለጫውን ለፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት በመላክ መናበብ ያስፈልጋል፡፡ የነእፓ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያወጡዋቸው ከወቅታዊ ጉዳዮች በተጨማሪ ማህበረሰቡን ግንዛቤ ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ አስተማሪ መልእክቶችን ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡ የክልል ቅርንጫፎች የአቋም መግለጫ ዝግጅት፣ የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት በሚያዘጋጀው ዝርዝር መሰረት ይፈጸማል፡፡

10) ***የንባብ ክበቦችን ስለማቋቋም፡*** ነእፓ የሀገራችን ወቅታዊም ሆኑ ነባር ችግሮች በእውቀት እና መረጃ ላይ በተመሰረቱ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ሊፈቱ ይገባል የሚለውን ድርጅታዊ ፍልስፍና በፓርቲው ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር የነእፓ አባላት በንድፈ ሀሳብ እና በተግባራዊ እውቀት የተገነቡ እንዲሁም በመልካም ስነምግባር የታነጹ ይሆኑ ዘንድ አባላት ጠንካራ የንባብ ባህል ሊያዳብሩ ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት ለአባላት ንባብ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይቻል ዘንድ በሁሉም የነእፓ ቅርንጫፎች የንባብ ክበባትን ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ የነእፓ የንባብ ክበባት አመሰራረት፣ አደረጃጀት እና አመራር ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ የነእፓን የንባብ ክበብ መመሪያ ከነእፓ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ከፓርቲው ዌብ ሳይት ማግኘት ይቻላል፡፡

## 13 የፓርቲው የውጭ ሀገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ይህ መመሪያ በውጭ ሀገር የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽቤቶችንም የሚመለከት ሲሆን፣ የውጭ ግንኙነት እና ዲያስፖራ የስራ ክፍል ተጨማሪ ዝርዝር መምሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14 ማህተም እና ደብዳቤ ልውውጥ

### 14.1 ማህተም አጠቃቀም

የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህጋዊ ማህተም በቅርንጫፉ ሊቀመንበሩ ወይም ሊቀመንበሩ በሚወክሉት የስራ አስፈጻሚ አባል እጅ ይቀመጣል፡፡

የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኃላፊ የቅርንጫፍን ማህተም ፈርመው ይቀበላሉ፡፡ የስራ ዘመናቸውን አጠናቀው ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ከኃላፊነታቸው ሲነሱ ማህተሙን ለተተኪ ኃላፊውም አስፈርመው ያስረክባሉ፡፡ በማህተም ርክክብ (መረከብ እና ማስረከብ) ሂደት እማኞች (ቢያንስ ሁለት) ርክክቡን ሊታዘቡ እና ይህንኑ በፊርማቸው ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ የፓርቲውን ህጋዊ ማህተም ከፓርቲው ህጋዊ እንቅስቃሴ ውጪ ለሌላ ዓላማ መጠቀም በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከባድ የሥነ ሥርዓት መተላለፍ የሚስቀጣ ሲሆን በህግም ያስጠይቃል፡፡ የማህተም ማስረከቢያ ቅ/ጽ በአባሪነት ተያይዟል፡፡

### 14.2 የደብዳቤ ልውውጥ

- የፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የስራ እንቅስቃሴ በቅርበት ለመረዳት እና ለማገዝ ይችሉ ዘንድ፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከማናቸውም ወገን ጋር የሚያደርጉትን የደብዳቤ ልውውጥ አንድ ቅጂ እንደ ጉዳዩ ይዘት ለዋና መስሪያ ቤት ወይም ለክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮፒ ያደርጋሉ፡፡ለዋና መስሪያ ቤት የተጻፉ ቅጅዎች እጅግ ቢዘገይ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አመቺ በሆነ የመላኪያ ስርአት (ፖስታ፣ ቴሌግራም፣ ፋክስ ወዘተ) ለዋና መስሪያ ቤት ይላካሉ፡፡
- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያደርጉት የደብዳቤ ልውውጥ ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቶት በፕሮቶኮል መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ የፕሮቶኮል ቁጥር አሰጣጥ ወጥነት ይኖረው ዘንድ በሚከተለው መንገድ ይሆናል፡፡

**FEP/ የክልል ወይም የዞን ስም/ተከታታይ ቁጥር፡፡**

1. አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/AA/001
2. ኦሮሚያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/OR/001 ይሆናል፡፡
3. ደቡብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/SPNNR/001 ይሆናል፡፡
4. ሀረር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/HR/001 ይሆናል፡፡
5. ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/DR/001 ይሆናል፡፡
6. ሶማሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/HR/001 ይሆናል፡፡
7. አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/HR/001 ይሆናል፡፡
8. አፋር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/AF/001 ይሆናል፡፡
9. ትግራይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/TR/001 ይሆናል፡፡
10. ጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/GMB/001 ይሆናል፡፡
11. ቤኒ ሻንጉል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/BSH/001 ይሆናል፡፡
12. ሲዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/SDM/001 ይሆናል፡፡
13. ደቡብ ምእራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደብዳቤ ቁጥር፡ FEP/SW/001 ይሆናል፡፡

**ማስታወሻ፡** ከዚህ የተለያየ የደብዳቤ ፕሮቶኮል ቁጥር መጠቀም የሚፈልግ ክልል ከፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ጋር መነጋገር ይችላል፡፡

## 15 የንብረት አያያዝ

የፓርቲው ንብረት የሆነ ማንኛውም ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረት በፓርቲው የንብረት አስተዳደር ስርአት መሰረት ሊያዝ ይገባል፡፡ የፓርቲው ቋሚ ንብረቶች ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቷቸው ሊመዘገቡ ይገባል፡፡

### 15.1 ህትመቶች/ጥራዞች

የሚከተሉት ህትመቶች ተዘጋጅተው በፓርቲው ውስጥ ሊኖሩ ይገባል፡

- የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ
- የወጪ ደረሰኝ

- የጥቃቅን ወጪዎች ማዘዣ ደረሰኝ
- የንብረት ገቢ ደረሰኝ

### 15.2 የጽ/ቤት መዝገቦች

በጽ/ቤቱ ውስጥ የሚከተሉት መዝገቦች ሊዘጋጁ ይገባል

- የማናጅመንት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ መያዥያ መዝገብ
- የአባላት መዝገብ
- የቋሚ ንብረት መዝገብ

## 16 ባለድርሻ እና ተባባሪ አካላት

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተቀመጡ የተለያዩ ስራዎችን ቅርንጫፎቹ ሙሉ ለሙሉ በራስ አቅም ወይም ከተለያዩ ባለድርሻ እና ተባባሪ አካላት ጋር በመተባበር ሊሆን ይችላል፡፡ በትብብር የሚሰሩ ስራዎች ለማከናወን እንደስራው አይነት የሚከተሉት ተቋማት ተባባሪ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላል፤

- የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሲቪክ ማህበራት፣
- ትምህርት ቤቶች እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣
- የሀይማኖት ተቋማት፣ እድሮች፣

## 17 የክልል/የዞን/የወረዳ/የከተማ አደረጃጀት

በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ እና በቀበሌ ደረጃ የሚዋቀሩ የፓርቲው አደረጃጀቶች በሚከተለው ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት ይቋቋማሉ፡፡




**<u>መግለጫ 1፡ የአባላት ብዛት</u>**

በእያንዳንዱ መዋቅር ላይ የሚመደቡ ኃላፊዎች ብዛት እንደ ክልሉ ህዝብ ብዛት እና ስፋት የሚወሰን ሲሆን የሚከተሉት የአባላት ብዛት እንደ መነሻ መጠቀም ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | መዋቅር | ጠቅላላ ጉባኤ | ምክር ቤት | ስራ አስፈጻሚ | ቋሚ ኮሚቴዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የክልል | 100-200 | 35 | 11 | 3-5 |
| 2. | የዞን | 75-150 | 25 | 9 | 3-5 |
| 3. | የወረዳ | 50-100 | 25 | 7 | 3-5 |
| 4. | ከተማ | 30-75 | 25 | 7 | 3-5 |
| 5. | የቀበሌ | 25-50 | 20 | 7 | 3-5 |

*መግለጫ 2፡ ቋሚ ኮሚቴዎችን ስለማደራጀት*

**የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን በተመለከተ፡** ከላይ የተመለከቱት በየደረጃው ያሉ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ብዛት ጠቋሚ ናቸው፡፡ የየምክር ቤቶቹ አባላት ቁጥር ከላይ ከተጠቀሱት ዝቅ ወይም ከፍ ሊል ይችላል፡፡ ትክክለኛው የምክር ቤት አባላት ቁጥር በአካባቢው ባሉ አባላት ይወሰናል፡፡

**ቋሚ ኮሚቴዎችን በተመለከተ፡** የክልሉ፣ የዞኖ፣ የወረዳው ወይም የከተማው አደረጃጀት በቂ የሰው ኃይል ካለው ከላይ የተጠቀሱትን ቋሚ ኮሚቴዎች በሙሉ ማደራጀት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በቂ የሰው ኃይል ከሌለ ከላይ ከተዘረዘሩት ቋሚ ኮሜቴዎች ውስጥ አንገብጋቢ የሆኑትን በቅድሚያ በማቋቋም፣ የቅርንጫፉ የስራ እንቅስቃሴ እየሰፋ ሲሄድ ቀሪ ቋሚ ኮሚቴዎችን በሂደት ማደራጀት ይቻላል፡፡

**18 መመሪያው የሚጸናበት ቀን**

ይህ መመሪያ በነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከጸደቀበት ከሰኔ 11፣ 2014 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሰኔ 11፣ 2014 አዲስ አበባ**
**አብዱልቃድር አደም (ዶ/ር)**
**ሊቀመንበር**

አባሪዎች

# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ

## ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

| ተ.ቁ | የስራ ዝርዝር | መግለጫ |
|---|---|---|
| | ሪፖርተ አቅራቢው ጽ/ቤት | |
| | ሪፖርቱ የሚሸፍነው ግዜ (ወር/ሩብ ዓመት) | |
| | | |
| I | የስራ ሪፖርት | |
| 1. | አዲስ አባላት ብዛት (የአባልነት ቅጽ አባሪ ተደርጓል) | |
| 2. | መታወቂያ የወሰዱ አባላት | |
| 3. | የማናጅመንት ስብሰባ ብዛት | |
| 4. | ህዝባዊ ስብሰባዎች | |
| 5. | የአባላት ስልጠና | |
| 6. | | |
| 7. | | |
| 8. | | |
| 9. | | |
| 10. | | |
| II | የፋይናንስ ሪፖርት | |
| *1.* | ካለፈው ወር የተላለፈ | |
| *2.* | ጠቅላላ ገቢ | |
| *3.* | ጠቅላላ ወጪ | |
| *4.* | ወደሚቀጥለው ወር የተላለፈ | |
| *5.* | | |
| *6.* | | |
| *7.* | | |
| *8.* | | |
| *9.* | | |
| *10.* | | |

# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ

## ማህተም ማስረከቢያ ቅጽ

**የተረካቢ ሙሉ ስም፡**________________________________________

**የቅርጫፍ ጽ/ቤቱ ስም፡**______________________________________

እኔ ስሜ ከላይ የተመለከተው በኃላፊነት የተረከብኩትን ማህተም፣

- በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት ለፓርቲው እንቅስቃሴ ብቻ የምጠቀም መሆኔን፣
- ማህተሙን የተጠበቀ ቦታ በጥንቃቄ የምይዝ መሆኔን፣
- የአገልግሎት ዘመኔ ሲጠናቀቅ ከኔ በኃላ ለሚመረጠው አስተባባሪ ወይም በቅርብ ለሚገኘው የፓርቲው የበላይ አደረጃጀት የማስረክብ መሆኔን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡፣

| የተረካቢ ስም እና ፊርማ | | የአስረካቢ ስም እና ፊርማ | |
|---|---|---|---|
| ስም | | ስም | |
| ፊርማ | | ፊርማ | |
| ስልክ | | ስልክ | |
| ቀን | | ቀን | |

<u>እማኞች</u>

| | ስም | ፊርማ | ስልክ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |